# ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ እንዳይሆን

ባጭር መንገድ መልክት ለማስተላለፍ ወይም አንድን ነገር ለማስረዳት የምንጠቀምባቸው በርካታ የቋንቋ ባህልዎች አሉን። በአማርኛ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ብሄረሰቦቻችን የቋንቋ ባህልዎች ማለቴ ነው ።ከእነዚህም አንዱ ይህ አረእስት ነው ።

ውሻን የማሳደግ ትርጉምና ባህል እንደማህበረሰቡ ይለያያል ። መዘረዘሩ ከአርእስቴ ጽንሰ ሃሳብ ስለሚያርቀኝ ወደዚያ አላመራም ። ከራሳችን ባህል አኳያ -ኢትዮጵያውያን ውሻን ከሚያሳድጉብት በርካታ ምክንያቶች ጥቂቶቹ ፥

- ሌባ እቤታቸው ቅጥር ግቢ ወይም ቤታቸው ውስጥ ገብቶ ሃብት ንብረታቸውን እንዳይዘርፍ - ለዘብነት
- እንደ ጅብ ዓይነቱ አውሬዎች ወደ ጋማና ቀንድ ከብቶች በረት ገብተው በቤት እንስሳት ላይ ጥቃት እንዳያደርሱ - በመከላከልና ጭሆ የቤቱ አባወራ ወይም ቤተሰብ እንዲደርስ ያደርጋል ብሎ በማስብ
- እንደ ተኩላና ቀበሮ አይነት አውሬዎች በግጦሽ ሜዳ ላይ ፍየሎቻቸውና በጎቻቸወን እንዳይበሉባቸው ለማስከልከል/ለማስጠበቅ
- ለሥጋ የሚፈለጓቸውን የዱር እንስሳት አሳደው እንዲዞላቸው
- እንደ ሚጥሚጣ ፣ ቃሬያ ፣ ዱባ ፣ጎመን የመሳሰሉትን የጓሮ አትክልቶች - ሚዳቆና ጃርት በመሳሰሉት እንስሳት እንዳይበሉ ለማስጠበቅ/ለማስከልከል

ዝንጉና ፈሪ ውሾች ጭሆት የሚያስሙት - ሌባውም የሚፈልገውን ዘርፎ ፣ ጅቡም ያማረውን እምቦሳ ወይም ጥጃ ፣ቀበሮም የመረጠውን ጠቦት  ይዞ ከሄዱ በኋላ ነው ። በመሆኑም

ምነው ፈሪ ውሻ አሳድጌ- ንብረቴን በሌብ አዘረፍኩ ወይም ጥጃዬን በጅብ አስበላሁ በማለት ቁጭትና ጸጸት ያሰማሉ ።

ይህ አርእስት በጅብና በውሻ ይመሰል እንጂ የበርካታ “ጸጸቶች” ተምሳሌት ነው ። በአራቱ የዓመቱ ወቅቶች መሰራት ያለባቸውን የግብረና ሥራዎች በቅጡ ካልተሠሩ- የምግብ እጥረት ያስከትላል። ከጅምሩ ያልተፈታ የቤተሰብ ችግር ቤተሰብ ያፈርሳል ። ሳይወሳሰብ ያልተፈታ የአገር ችግር ለመፍትሄ ያስችግራል ። የአንድን ህመምተኛ በሽታ በጊዜ ካ

ታወቀ ለማዳን ያውካል ። ባጠቃላይ ይህ አርዕስት - በድንቁርና ፣ ባለማስተዋል ፣ ባለመገንዘብ ፣ በሥንፍና ፣ ባለመንቃት፣ በቸለተኝነት ወዘተ ስላጠፉነው ወይም ስላጠፉናቸው ጥፋት/ቶች -የህሊና ጸጸት/ቶች ነፀብራቅ ነው ።

ይህ በዚህ እንዳለ ትቼ እስቲ ይህ አርእስት ላስተላልፍበት ወደ ምፈልገው ቁም ነገር ላምራ ፤የኑግሥ ኃይለሥላሴ ፍጹም ዘውደኛና የደርግ ፋሽስታዊ የአገዛዝ ሥራዓቶችን አስወግዶ - ሁላችንም በእኩልነት በሚያስተዳርና ሁላችንም በእኩልነት በሚዳኝ ዲሞክራሲያዊ ሥራዓት ለመተካት በተደረጉትን በኢትዮጵያ ተማሪዮች ንቅናቄዎችና ሕዝባዊ አመጽዎችን ታግሎ በማታገል ግንባር ቀደም ሚና ሲጫውቱ ተጉዘው ፤ እ.አ.አ 1970 ዎች አጋማሽ ማንንም የኢትዮጵያ ብሄረስብ ያላገለልና ኅብረብሄር የፖለቲካ ድረጅት መሠረቱ።

ከዚያም የትግሉን እስትራተጂ፣ስልትና እምርታ ለምሳደግና ከደርግ እመቃ ለመቋቋም የፖለቲካ ትግሉን በትጥቅ ትግል እንዲታገዝ አድርጉ።ስለሆነም በፖለቲካውና በትጥቅ --ታግለው በማታገል እያሉ ፤(ሀ) ከየሃገራችን ከተሞችና ገጠሮች ከደርግ ቁንጮ ከፋሽሲቱ መንግሥቱ ጭፍጨፋ አምልጠው ወደ ባእዳን አገሮች የተሰደዱትን (ለ)በሰሜኑ የሃገራችን ምድሮች በደፈጣ ትጥቅ ትግል እየተፋለሙ እያሉ ፤ በኪዩባ፣ በረሺያ፣ በምሥራቅ ጀርመንና

በሌሎች የሶሻሊስት አገሮች ትጥቅና ስንቅ በታጀበው ፋሽስቱን መንግሥቱ ሠራዊት (ሐ) በዚያድ ባሬ፣በሱዳን፣በአረብ አገሮች ፣በአሜሪካና በምዕራቡ አገሮች መንግሥታት ትጥቅና ስንቅ በታጀቡትን ከወያኔና ከሻቢያ ሠራዊት ከበባና ምት- ከሞት ተርፈው ወደ ባዕዳን አገሮች የተሰደዱትን የዚያ ትውልድ አንጋፋ የለውጥ አርበኞች፤ በአካል ከአገራቸው ይራቁ እንጂ ፤ በመንፈስ ፣በኅሊናና በስነልቦና ከሀገራቸውና ከሕዝባቸው ጋር ስለሆኑ ፤ የአሀገራቸውና የሕዝባቸውን የወደፊት እጣፋንታ ምን እንድሚሆንም ይታያቸው ስለነበረ ፤ በተሰደዱ ማግሥት ሳይውሉ ሳያድሩ በየደረሱበት ተደራጅተው መታገል ጀመሩ ።

ኢትዮጵያውያን የመታገያና የመሰባሰቢያ ምርጫ እንዲኖራቸው በማሰብ ፤ የፓሪስ አንድና ሁለት ፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) ፣ የአማራጭ ኃይሎች ፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) እና የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል (ሸንጎ) የመሳሰሉትን ድርጅቶች በየተራ እንደሁኔታውና እንደ አስፈላጊነታቸው መሥረቱ ።

ህወሃት የደርግ ቁንጮ ፋሽስቱን መንግሥቱ አሸንፎ እግሩን አዲስ አበባ ካስገባበት 1983 ዓ/ም ጀምሮ ፤ ህወሃት ሥልጣን ላይ ከቆየ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ህልውና አደጋ የከፋ እንድሚሆንና አሁን በተጨባጭ የምናያቸውና የምንሰማቸውን ሁኔታዎች እንደሚከሰቱ ጠንከር አድርገው አሳስበዋል ፤ቀስቅሰዋል ፤አስገንዝበዋል ፤ጽፈዋል ።

አንድ ተቋዋሚ የፖለቲካ ቡደን ብቻውን ታግሎ ወያኔን አሸንፎ የፖለቲካ ሥልጣን መጨበጥ እንደማይችልም ፤ ከሃያ አራት ዓመት በፊት ታይቷቸው ፤ 'ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር' እባካቹሁ ፀረ ህወሃት ህብረት ፈጥረን እንታገል ፤ ጊዜ ሳንሰጥ አገራችንና ሕዝባችን ከወያኔ መንጋጋ እናውጣ ብለው ከመለመንና ከመማጸን ተዘናግተው/ ተቆጠበው

አያውቁም ። ነቢይ በአገሩ አይከበርም ፤ አይደመጥም ፤ እንደሚባለው  ሰሚ አጥተው እነሆ የአገራችን ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግሮች ወደ ተወሳሰበ ቀውስ እያመሩ ይገኛሉ ።

ከላይ ያሰፈርኩትን አንቀጽ 'ሃሳባ' የማይወዱና አዎን የማይሉ እንዳሉ ባውቅም - ፀሃይ የሞቀው ሃቅ በመሆኑ -ይህንን እውነት በማስጨበጤ የኀሊናም የታሪክም ተመስጋኝ እንጂ ተወቃሽ እንደማልሆን አውቀዋለሁ ።

በምጣኔ ሃብት የበለጸጉ አገሮች መንግሥታትና ሕዝብ ትልቅ ነገር ማሰብና ትልቅ ነገር መሥራት ካስቻሏቸው ሁኔታዎች አንዱ ፤ በተለያዩ የሞያ ዘርፎች የሠለጠኑትን ሞያተኞቻቸውን ሊሂቅነት (ኤክስፐርቲስ) ምክርና መመርያ ስለሚከተሉ ነው ።

በዘመነ ወያኔ በአገር ቤትና በባእዳን አገሮች እንድ አህያ ፈስ እንጉዳይ በአንድ ጊዜ ብቅብቅ ያሉትን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፣ የሲቪክና የሰባዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅትች ፤ የህብረት ጥሪዮችን እምቢ ያሉበት ምክንያቶች በርካታ ናቸው ፤ ከእነዚህም ጥቂቶቹ ፡-

- እውነትም የነኚህ አንጋፋ ታጋዮች የፖለቲካ ንቃትና ብስለት ከሌሎች ተቃዋሚዎች ላቅ ያለ ፣ አርቆ የሚያይና የቀደመ በመውሆኑ ሊርዱላቸው ወይም ሊገነዘቡላቸው ባልመቻል ፤

- ባወቅኩሽ ናቅኩሽ ፤ እኔ ከእነሱ እሻላለሁ ወይም እበልጣለሁ ፤ በተናጥል ታግዬ ለሥልጣን እበቃለሁ በባይነት፤

- በተቃዋሚ ስም የወያኔን ዕድሜ ለማራዘም የሚሠሩ በመኖራቸው ፤

- በባዕዳን አገሮች ከተደራጁትን የፖልቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ጋር ህብረት ከመፍጠር ከውያኔ ጋር መደራድርና ወያኔን ማጠናከር ይሻላል ባይ የፖለቲካ ድርጅቶች ስለነበሩ ፤

- በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ሕልውናና ጥቅም ላይ በፍጹም ከማይደራደሩትን ሃቀኛ ታጋዮች ጋር ህብረት ከመፍጠር -የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕልውናና ጥቅም ከሚጻረሩና ከሚፈታተኑትን ጋር መተባብርን የመረጡ የፖለቲካ ድርጅት/ቶች በመኖራቸው/ስላሉ ፤ ድርጅቴ የሰባዓዊ መብት ጥሰት ተሟጋች ስለሆነ ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ህብረት ለመፍጠር የድርጅቴ ባህሪ አይፈቅድልኝም በሚል ስበብ ። የኢትዮጵያውያን ሰባዓዊ መብት ለማስከበር በሚል በተለያዩ በምጣኔ ሃብት በበለጸጉ - ባዕዳን አገሮች የተደራጁትን አንዳንድ ድርጅቶች - ከተመሠረቱባቸው አገሮች መንግሥታት በሚያገኙትን የግንዘብ እርዳታ( ፈንድ) ስለሚተዳደሩ - በኢትዮጵያ ዲሞራሲያዊ ሥራዓት ቶሎ እንዲመጣ አይፈልጉም ። በተለያዩ ሰላማዊ ሰልፎች፣በተለያዩ የመንግሥትታ ሰብሰባዎች ፣ በተለያዩ ኢ-መንግሥታት ሰብሰባዎች በመገኘት እና ለተለያዩ የዜና አውታሮች እየቀረቡ የአዞ እንባ ሲያነቡ ይታያሉ ፤ ይድመጣሉ ። እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች - ጆርጅ ኦርዌል (የድኅረ ኢንዱስትሪ ሥልጣኔና የድኅረ ኢንዱስትሪ ከበርቴ ዘመን - አስመሳይ ስበዓዊያን /ሁማኒስት) ይላቸዋል ።

ህወሃት ቀደምቶቹ የኢትዮጵያ ገዢዮች ማአከል የአዲስ አበባ ቤተገዢዮች (ቤተ መንግሥት) መቀመጫው ካደረገበት 1983 ዓ.ም ጅምሮ በርካታ አንጻራዊ ጠመንጃ አልባ ፀረ-ህወሃት አምጾች ተደርገዋል እዮተደረጉም ነው ። ከጥር ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ በተለይም ከጥር 6-8 የኦሮሞ ብሄረስብ የክልልን መብት አስመልክቶ ያደረጉትን ሕዝባዊ አመጽ ከዚያ በፊት ከተድረጉትን ሕዝባዊ ሰላማዊ አመጾች ሁሉ የላቀና አስፈሪ ስለነበረ ፤ ከእነኚህ በባዕዳን አገር ከተደራጁት አንዳንድ ለኢትዮጵያውያን ሰባዓዊ መብት ተሟጋች ነኝ ከሚሉትን በስተቀር ፤ ከላይ የጠቀስኳቸው ዓይነት የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች መሪዮች በሙሉ እጅግ በጣም እንዳስደነገጣቸው ለተለያዩ ኢትዮ -ድረገጾች ከሚጽፉት ጽሑፎችና ለተለያዩ ኢትዮ-

ዜና አውታሮች ከሚሰጡት የቃለመጠይቅ መልሶችና አስተያይቶችን ቃና (ቶን) መረዳት ቼያለሁ ።

## ምክንያቱም

1.በንቃተ ኅሊና ማነስ ምክንያት ወይም ባለማወቅ የኅብረት ትግል ጥሪ ላ ተቀበሉት- የተከሰተው ሁኔታ ማለት አመጹ- ከሰማይ የወረደ ድቡዳ ወይም ቁጣ ስለመሰላቸው ።

2. ባወቅኩሽ ናቅኩሽ ፤ እኔ ከነ እገሌ እሻላለሁ ፤ በተናጥል ታግዬ ለሥልጣን እበቃለሁ ባዮች ፤ ወያኔ ወድያውኑ ወድቆ ያ ሲመኙት የነበረውን ሥልጣን ጭራሽ ባላሰቡት ኃይሎች እጅ ይወድቃል ብሎ በመሥጋት ።

3. በተቃሚ ስም የወያኔን እድሜ ለማራዘም የሚሠሩ ድርጅቶች - ወያኔ እያለቀለት ነው ! ምን ይዋጠን ! መደበቂያችን የት ይሆን ! ብለው በመጨነቅና በመርበትበት ።

4.በባዕዳን አገሮች የተደራጁትን የተቃዋሚ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች አግልለው ከወያኔ ጋር የተደራደሩትን የፖለቲክ ድርጅቶች ፤ እንደ እነዚህ ዓይነት ጠላትን ወዳጅ ፤ ወዳጅን ጠላት በማድረግ የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ የነበራቸውን ተሥፋ የጨለመ መስሎ በመታየቱ ፤ ወያኔ ወዲያውኑ ወድቆ የፖለቲካውን ሥልጣን ባላሰቡት ኃይሎች እጅ የሚወድቅ ስለመሰላቸው ።

5.ወያኔን አስወግደው በኢትዮጵያ ዲሞራሲያዊ የመንግሥት ሥራዓት መሠረት ለመጣል - የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕልውናና ጥቅም ከሚጻረሩትና ከሚፈታተኑትን ጋር ህብረት የፈጠርሩትን ድርጅት/ቶች ፤ የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪ እንደሚባለው

-ከየትም የትም አተራምሰው ባጭር አቋራጭ ሥልጣን ለመጨበጥ የነበራቸውን ምኞትና ጉጉት ስላጨለመባቸው ።

ሁኔታው ከእነሱ የፖለቲካ ስሌት ውጭ ሆኖ ስላገኙት ።

ይህ በዋናነት የኦሮሞ ብሄረሰብ ወጣቶች በተከታታይ ያደረጉትን ሰላማዊ አመጽዎች የፈጠረው ሁኔታ ከላይ ከ 1 -5 የጠቀስኳቸው ዓይነት ድርጅቶች መሪዮች የተጓዙበትን የትግል ፤ እይታ፣ ስክነት ፣አሰላለፍና ስልት ደግመው ደጋግመው እንዲያስቡበትና እንዲመረምሩ የሚያስገደዳቸው ይመስለኛል ።

ለሃያ አራት ዓመታት - ለህብረት ትግል አቤቱታና ወትወታ ጆሮ ዳባ ማለት ውጤቱ ምን እንደሆነ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዮች በተጨባጭ ትምህርት ያገኙበት ይመስላል ። የፖልቲካ የዋህነት (ናይቪቲ) ፣ ከማን አንሳለሁ ብቻዬን ታግዬ ለሥልጣን እበቃለሁ ባይነት ፣ ተቃዋሚ መስሎ ለወያኔ መቆም ፣ ባጭር አቋራጭ ሥልጣን ለመጨበጥ -ሃቀኛ ታጋዮችን አግልሎ ከባንዳዎች ጋር መሰለፍ ወዘተ..ለጥፋት እንጂ ለየትኛውም አገርና ሕዝብ አድን ፖለቲካ ግብ እንደማያደርስ ትምህርት ያገኙበት ይመስለኛል ።

አገርና ሕዝብ አድን ትግል ለማጠናከርና ለማፋጠን ፤

(1) በታጋዮችና በድርጅቶች መካከል መለስተኛ ቅራኔዎች ካሉ በአስቸኳይ በውይይት መፍታት

(2) የአገርና የሕዝብ ፍቅር ከ አለኝነትና ከድርጅታዊ ፍቅር ማስቀደም

(3) የወል ትግሉ አካል ከሆንኩ - ሊ/መንበርነቴ ፣ ዋና ጸሃፊነቴ ፣ ገንዘብ ያዥነቴ ወዘተ..ዓይነቱ ተክለሰውነት (እስተሳስብ ሲምቦል) አጣለሁ/እነጠቃለሁ

ከመሳሰሉት ፍርሃትና አስተሳሰብ መላቀቅ ፤ አገራችንና ሕዝባችን ካሉበት ቀውስ/አደጋ ፣ ለማዳን ለሚደረገው የጋራ ትግል - በተላላኪነት ፣ በቢሮ ጠራጊነት ፣ በቡና/ በሻይ አፍሊነትም ወዘተርፈ ቢሆንም ለማገልገል የተዘጋጀን መሆን አለብን ፤ ማለት ለምን ከፍ ያለ ቦታ አልተሰጠኝም ማለት የለብንም (ሰልፍለስ) መሆን አለብን (4) ቁሳቁሳችንን፣ ገንዘባችንን ፣ ሥነልቦናችንን ፣ ጉልበታችንን ፣ፀሎታችንን ፣ የፖለቲካ እውቀታችንን ወዘተ.. ማገናኘት (5) ትግሉን እኔ ካልመራሁት ፣እኔ በምፈልገው መሥመር ካልሄድ -ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ባፍንጫቸው ይደፉ ባዮችና ትግሉን እንዳይሳካ እንቅፋት በሚፈጥሩትን የፖለቲካ ሴረኞች ላይ እቀባ ማድረግ ።

በዚህ ጽሑፍ ከላይ እንደጠቆምኩት በተለያዩ ጊዚያት በዓይነትም በመጠንም የተለያዩ ዱላ አልባ ፀረ-ህወሃት ሕዝባዊ አመጾች ተሞክረው እዳር ሳይደርሱ ከሽፈዋል ። ለምን ? የኢትዮጵያ ሕዝብ ለውጥ ስላልፈለገ ? የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው ንቃተ-ኅሊና ለትግል ብቁ ባለመሆኑ ? ነባራዊ ሁኔታዎች ስላልተሟሉ ? የኢትጵያ ሕዝብ ፈሪ ስለሆነ ? ወዘተ.. መልሱ አጭር ነው ፤ ይኸውም የአገራችን የወቅቱ ሁኔታ ያገናዘበና የወቅቱ የሃይልሚዛን የሚመጥን የትግል እስትራተጂና ስልቶች ያዘጋጀ ጠንካራ የህብረት ድርጅትና ጠንካራ መሪ/መሪዎች ስላላገኙ ነው ።እነዚህን ብቅ ድርግም አመጾች -ቅድመ ‘ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት’ አመጽ/አመጽዎች ጠቋሚ(ሲምተም) ናቸው ።

ያንን ከብቶች በጅብ ካስጠቃ በኃላ የጮኸው ውሻ - ከጌታው ወይም ካሳዳሪዩ ቅጣት ፣ ተግሳጽና ምክር ስልተሰጠው ፤ ያንን ዓይነት ሥህተት ላለመድገምና ነቅቶ ለመጠበቅ ተዘጋጀ ። ስለሆነም ከዚያ በኋላ ጅቡም ወደ ከብቶች በረት ሳይጠጋ ፤ የሰው ሌባም ወደ ቤት

አጥር ሳይጠጋ ፤ በሩቅ እያሉ ጠረናቸውን በማሽተት ጭሆ - አሳዳሪውን ወይም ቤተሰብ ነቅቶ በተጠንቀቅ እንዲቆዩ ያደርግ ጀመር ።

እኛም ካለፉትን 'ጅብ ከሄድ ወሻ ጮኸን' ስህቶቻችን ተምረን፣ተጸጽተንና ተቆጭተን ፤ አስተማማኝ እስትራተጂ፤ ስልቶችና መሪዎች (ሊደርሺፕ) ያሉትን/ያቀናጀ ጠንካራ የህብረት ድርጅት ፈጥረን፤ በመጪዎች- እምቢልታ እያሰሙ በሚመጡት መሬት አንቀጥቅጥ (ቢግባንግ) ሕዝባዊ አመጽዎች፤ ወያኔ አንኮታኩተን ጥለን ፤ሀገራችንም ከመፍረስ ፤ ሕዝባችንም ከመከራ ለማዳን በጽኑ መዘጋጀት አለብን ። ያ ካልሆነ ሁሌ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸን እሮሮ እያሰማን ልንኖር ነው ማለት ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተባበረ ክንዱ ወያኔን ድባቅ ይመታል!

ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ኅልውናና ነጻነት አልፋና ኦሜጋ ናቸው !

ታጠቅ መንጂ

19 January 2016